# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 354 የካቲት 13 2007 ገጽ


አርበኞች ግንቦት 7፡ የአንድነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በህወሓት ወታደራዊ ሰልፍ እና የመሣሪያዎች ትዕይንት የሚረበሽ ድርጅት አይደለም። ይልቁንም በሰልፉ ጨኸት የታፈነው የኢትዮጵያዊ ወታደር ጩኸት ይሰማዋል። ኢትዮጵያዊ ወታደር በአዛዦቹ ላይ ጥርሱን ነክሶ፣ ቂም አርግዞ ሰልፋቸውን እንደሚሰለፍ አርበኞች ግንቦት 7 ያውቃል። አርበኞች ግንቦት 7፣ የሠራዊቱ አባላት ውስጥ ውስጡን እየተሰቃዩ የታዘዙትን መፈፀማቸው መብቃት አለበት ይላል፤ ወይ ተቀላቀሉን፣

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ፕሬዜዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ወያኔ ሲሰነዘርባቸው የቆየውን ታሪክን የማጠልሸት ሴራ በተመለከተ ለኢሳት ተናገሩ

*ዘረኛው የህወሃት አገዛዝ በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝቦች መካከል የዘራው የጥርጣሬና የጥላቻ መርዝ በሁለቱ ህዝቦች ታሪክ ውስጥ ያልታየ ነው ሲሉ የተናገሩት ፕሬዜዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ፤ ይህም በሁለቱ ህዝቦች ላይ የተፈጸመ ወንጀል ነው ብለዋል።*

የኤርትራው ፕሬዜዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ከኢሳት ቴሌቭዥን ጋር በነበራቸው ቆይታ ባለፉት 24 አመታት በዘረኛው የህወሓት አገዛዝ ሲሰነዘርባቸው የቆየውን ታሪክን የማጠልሸት ሴራ በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን አያይዘውም የነበረው የታሪክ መዛባትና ውዥንብር ሊጠራና የቀደመው ግንኙነት ሊመለስ ይገባዋል ሲሉ ለሁለቱ አገራት ህዝቦች መልዕክት አስተላልፈዋል።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተፈጠረው ችግር በኢትዮጵያ ስልጣን የያዘው አናሳና ዘረኛ ቡድን ትልቅ አገር በመቆጣጠሩ ሳቢያ አስተሳሰቡ ያስከተለው መዘዝ እንደሆነ ያመለከቱት ፕሬዜዳንት ኢሳያስ በኢትዮጵያ በኤርትራ ህዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ማንኛውም የፓለቲካ ሃይል ወይም ማንኛውም መንግስት እንደፈለገው ሊጠመዝዘው የሚችለው ነገር አለመሆኑን በመጥቀስ አሁን ዘረኛው የህወሃት አገዛዝ ያሰፈነውን የታሪክ መዛባት እልባት ልናብጅለት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል። የወደፊቱን እንመልከት ያሉት ፕሬዜዳንት ኢሳያስ በዘረኛው የህወሃት አገዛዝ የተዘሩት የጥላቻ፤ ጥርጣሬ እና ግጭት ሴራዎች ታርመው ወደ ቀድሞ የነበረው ሁኔታ ለመመለስ በጋራ ልንሰራ ይገባል ብለዋል።

...... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ መጭውን የ2007 ዓ.ም የይስሙላ ምርጫ በተመለከተ ተናገሩ

*የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በየ 5 አመቱ እያካሄደ ያለው የይስሙላ ምርጫ ምንም አይነት ለውጥ በአገራችን ሊያመጣ እንደማይችል የተናገሩት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘረኛውን የህወሃት አገዛዝ በህዝባዊ እምቢተኝነትና ህዝባዊ አመጽ ከጫንቃው አሽቀንጥሮ ለመጣል በጋራ እንዲነሳ ጥሪ አቅርበዋል*

የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከሬዲዮ ክፍላችን ጋር ባደረጉት ቆይታ ዘረኝው የወያኔ አገዛዝ በየ 5 አመቱ እያካሄደ ባለው የይስሙላ ምርጫ ቅንጣት ያክል ለውጥ ሊመጣ እንደማይችል በመግለጽ ይልቁንስ በአርበኞች ግንቦት 7 የተነደፉትን የትግል ስልቶች ማለትም ህዝባዊ እምቢተኝነትና ህዝባዊ አመጽ እንዲቀላቀሉ ጥሪ ጥሪ አቅርበዋል። በዘረኞቹ ህወሓቶች ሙሉ ቁጥጥር ስር በሚካሄድ ምርጫ ኢትዮጵያን የሚጠቅም ለውጥ ሊመጣ ይችላል የሚለው እምነት ለአርበኞች ግንቦት 7 ፈጽሞ የተሟጠጠው ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ መሆኑን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አስታውሰዋል። የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በቅርቡ በሰላማዊ ትግል በምርጫ አገዛዙን ለመጣል በሚንቀሳቀሱት የአንድነትና መኢአድ ፓርቲዎች ላይ ያደረሰውን ውንብድናና ፍጹም አረመኔያዊ የሃይል እርምጃ አገዛዙ በሰላማዊ ትግል ወይንም በምርጫ ሊወገድ እንደማይችል በድጋሜ ያረጋገጠበት እንደሆነ አመልክተዋል።

የተከበራችሁ አድማጮቻችን ከንቅናቄያችን ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር ያደረግነው ቆይታ በዛሬው ፕሮግራማችን የተካተተ በመሆኑ የምናስደምጣችሁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን።

## የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝን በትጥቅ ትግል የሚያምኑ ለማስወገድ የሚንቀሳቀሱት ሶስቱ የአፋር ድርጅቶች ግንባር ፈጠሩ

በስልጣን ላይ ያለውን ፋሺስታዊ የህወሃት አገዛዝ በጠመንጃ ለማንበርከክና ለመገርሰስ የሚንቀሳቀሱት ሶስቱ የአፋር ድርጅቶች ማለትም አርዱፍ፣ ጋድሌና የአፍዴራ ታጋዮች የካቲት 8 ቀን 2007 ዓም የጋራ ግንባር መፍጠራቸው ታውቋል። የአርዱፍ ሊቀመንበር አቶ ኢብራሂም ሙሳ እንደተናገሩት ሶስቱም የአፋር ድርጅቶች በተናጠል ሆነው መዋጋታቸው ለስርአቱ እድሜ መርዘም አስተዋጽኦ በማድረጉ በቅድሚያ ድርጅቶቹ የጋራ ግንባር ፈጥረው በጋራ ለመዋጋት አስፈላጊ መሆኑን ስምምነት ላይ በመድረሳቸው፣ በአንድ ወታደራዊ እዝ ስር ሆነው ለመታገል ወስነዋል ብለዋል። አዲሱ ግንባር ከሌሎች የኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር ጥምረት በመፍጠር ለመታገል ፍላጎት እንዳለውም አቶ ኢብራሂም ተናግረዋል።

## የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ሙስሊሞችን በዘመቻ መልክ እያፈሰ ወደ እስር እያጋዘ መሆኑ ታወቀ

*በህዝበ ሙስሊሙ ፍጹም ሰላማዊ ተቃውሞ የተብረከረከው ፋሺስታዊ አገዛዝ በአዲስ አበባ ብቻ ከ800 -1000 የሚደርሱ ንጹሐን የእምነቱ ተከታዮችን ለማሰር አቅዶ ዘመቻ መጀመሩ ታውቋል*

አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከመጪው የግንቦት ወር የይስሙላ ምርጫ ጋር በተያያዘ በህዝበ-ሙስሊሙ መካከል ትልቅ ንቅናቄ ይፈጥሩ ይሆናል የሚል ስጋት ያሳደሩ ሙስሊሞች በጅምላ እየታደኑ ወደ እስር እየተጋዙ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል። በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች የአሰሳ እና ስምሪት ተግባር እየተካሄደ ሲሆን፤ በተለይ በአዲስ አበባና በጅማ በርካታ ሙስሊሞችን በጅምላ የማሰሩ ዘመቻ ተጠናክሮ እየተካሄደ እንደሚገኝ ታውቋል። ሙስሊሞቹ በተያዙበት አካባቢዎች በወደሚገኙ የፖሊስ ጣብያዎች እየታጎሩ ሲሆን፤ የመኖሪያ ቤታቸውም በፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ፖሊሶች እና ደህንነቶች እየተፈተሸ እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ቤታቸው የሚገኙ የተለያዩ ላፕቶፕ እና የግል ንብረቶቻቸውም “ለምርመራ ያስፈልጋሉ” እየተባሉ መወሰዳቸው ታውቋል።

ፍጹም ሰላማዊው ሕዝበ ሙስሊም ለእምነቱ ነፃነት እያደረገ ባለው ተጋድሎ ከትግሉ ጅማሮ አንስቶ በተደጋጋሚ በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ህገ ወጥ የእስር ዘመቻዎችን ጨምሮ ግድያ፤ ድብደባና ማሰቃየት ሲፈጸምባቸው የቆየ ሲሆን ይህም አገዛዙን ከግድያ፤ እስርና ከሃይል እርምጃ በስተቀር ለችግሩ መፍትሄ ወይም እልባት የመስጠት የሞራል አቅም የሌለው መሆኑን በተደጋጋሚ አሳይቷል። እንደ አዲስ የተጀመረው ህገ ወጥ የእስር ዘመቻ ‹‹ትግሉን በጉልበታችን አስቁመናል›› ሲሉ እየደረሰኮሩ ለነበሩ የወያኔ ቱባ ሹማምንት ትግሉ አሁንም ተቀጣጥሎ ያለ የህዝብ አደራ መሆኑን ሳይወዱ በግድ ያሳበቀባቸው እውነታ እንደሆነ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ በስፋት እየተነገረ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። ንፁህንን ከቤት እያፈኑ ወደ እስር እያጋዙ ማጎርና ማሰቃየት ፍጹም አምባገነናዊ የሆነ አገዛዝ መገለጫ ነው ያሉት ሙስሊም ምእመናን የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በጠራራ ፀሀይ እየፈፀመ ካለው እጅግ አስነዋሪ ወንጀል፤ የሰብዓዊ መብትን በአደባባይ የሚረግጥ ህገ ወጥነት በመሆኑ ከእኩይ ተግባሩ በአስቸኳይ ሊታቀብ ይገባዋል ሲሉ እየጠየቁ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል።

## በኦሮሚያ ክልል ቱባ ሹማምንት መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ተካሮ መቀጠሉ ታወቀ

በኦሮምያ ክልል ቱባ ሹማምንት መካከል ከጥቅም ጋር በተያያዘ የተፈጠረው አለመግባባት ወደ ተካረረ ደረጃ መድረሱ የታወቀ ሲሆን አለመግባባቱ በኦሮሚያው የጥፋት ክንፍ በሆነው ኦህዴድ ህልውና ላይ አዳጋ ጋርጦበት እንደሚገኝ የውስጥ ምንጫችን ያደረሰን መረጃ ያሳያል። ውስጥ ለውስጥ እየተብላላ የቆየው አለመግባባት ወደ ተካረረ ደረጃ መድረሱን ተከትሎ ቱባ ሹማምንቱ በአደባባይ መዘላለፍ መጀመራቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ከሰሞኑ ክልሉን በሙስናና በመልካም አስተዳደር እጦት እንዳቆረቆዘው የሚነገርለት አባ ዱላ ገመዳ ከአሁኑ የክልሉ የወያኔ ቱባ ሹም ሙክታር ከድር ጋር በግምገማ ወቅት በይፋ መሰዳደባቸውን ለማወቅ ተችሏል። በሹማምንቱ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በግልጽ አንጃዎችን ፈጥሮ መቀጠሉ ለድርጅቱ ህልውና ስጋት ሆኖ መቀጠሉም ታውቋል። ከአሁኑ የክልሉ ሹም ሙክታር ከድር በፊት ክልሉን ሲመራ የነበረው ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አዋራጅ ሰልፎችና ድግሶች እንዲያበቁ ህወሓት ይወገድ !

ድግሶችን፣ ወታደራዊ ሰልፎችንና ህውልቶችን ማብዛት የአባገነኖች ሁሉ የጋራ ባህርይ ነው። ዘረኛውና ፋሽስቱ የህወሓት አገዛዝም በሕዝብ እየተጠላ፣ እያረጀና እየወላለቀ በሄደ መጠን በየተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ደግሶ መብላት፤ ወታደራዊ ሰልፍና የመሣሪያ ጋጋታ ማሳየት እና በየመንደሩ ሀውልት መመረቅ ሙያው አድርጎት ቆይቷል።

የህወሓት ድግሶችና ፌሽታዎች የአገራችን ሀብት ከማሟጠጣቸውም በላይ የመንግሥት ሠራተኞችን፣ የአርሶ አደሮችንና የአነስተኛ ነጋዴዎችን ኪስ እያራቆቱ ናቸው። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ተወላጆች በእስር ቤቶች እየማቀቁ በሚገኙበት ሁኔታ፤ በመቶ ሺዎች የሚገመቱ የአማራ አርሶአደሮች ተፈናቅለው እያለ፤ በጋምቤላና በኦጋዴን ወገኖቻችን ላይ ዘግናኝ የጅምላ ጭፍጨፋዎች እየተደረጉ፤ በአፋር፣ በሲዳማ፣ በቦረና፣ በወልቃይት እና በመላው ኢትዮጵያ ግጭቶች በበዙበት፤ ሕዝብ እያለቀሰ ባለበት በአሁኑ ሰዓት "የብሔር፣ ብሔረሰቦች መብት ተከበረ" እያሉ እነዚህኑ በደል እየደረሰባቸው ያሉ ዜጎችን ማስጨፈር እና ለእነዚህ ጭፈራዎች በርካታ ሚሊዮኖች ብር ማውጣት በእጅጉ ያስቆጫል። እነዚህ ጭፈራዎች ለህወሓት ሰዎች የገቢ ምንጮች መሆናቸው ጥርጥር የለውም፤ ለድህው ኢትዮጵያዊ ግን መራቆቻዎች ናቸው። ከዚህም አልፎ በዘረኝነት እየተበደለ ያለ ሕዝብ ስለእኩልነት ዝፈን ማለት ክብረ ነክ ተግባር ነው። ዘንድሮ በአሶሳ የተደረገው አገር አቀፍ ድግስ ካለቀ ጥቂት ወራት በኋላ አገራችን በሌላ ዙር የህወሓቶች ድግስ ተወጥራለች።

ሰሞኑን በባህር ዳር በተደረገው የጦር ሠራዊት ሰልፍ እና ሰልፉን ተከትሎ በነበረው የድግሶች ግርግር ከሁሉም በላይ የተሰደበውና የተዋረደው የሠራዊቱ አባል ነው። አዛዦቹ መቶ በመቶ የህወሓት አባላት የሆኑበትን ሠራዊት "የኢትዮጵያ መከላከያ" ተብሎ መጠራቱ ራሱ የሚያሳፍረው ኢትዮጵያዊ ወኔ በልባቸው ውስጥ እየተንቀለቀለና እልህ እየተናነቃቸው ያሉ የሠራዊቱን አባላት ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት እንዴት የኢትዮጵያ ጠላቶች በሆኑ የህወሓት ካድሬዎች ይመራል? እንዴት የአስር አለቃ እንኳን ሊሆን የማይገባው የህወሓት ካድሬ "ጄኔራል" ተብሎ ኢትዮጵያዊያን ወታደሮችን እንደ ሎሌው ያዛል? እንዴት አንድ የህወሓት ሎሌ ሹመት ተሰጥቶት እየፏለለ በልምድ፣ በትምህርትና በእውቀት የሚበልጠውን ኢትዮጵያዊ ተንቆ ይዋረዳል? ይህ ቁጭትና እልህ ሠራዊቱ የዘረኛውን ህወሓት ሰልፍ አድማቂ መሆኑ የሚያከትምበት ጊዜ ይበልጥ እንዲናፍቅ የሚደረገው ነው። አልያማ ሰልፍ ያሳመረ ሠራዊት ሁሉ አሸናፊ እንዳልሆነ የታወቀ ነው። በሰልፍ ብዛትና በመሣሪያ ትዕይንት ማሸነፍ ቢቻል ኖሮ የትም አገር አምባገነኖች ባልወደቁም፤ ህወሓት ራሱን ስልጣን ላይ ባልወጣም ነበር።

የህወሓት ምሥረታ 40ኛ ዓመት ድግስም ሌላው የታሪክና የሀብት ውድመት የሚያስከትል ክስተት ነው። የካቲት 11 ቀን 1967፣ ጥቂት ኢትዮጵያዊያን እናታቸውን ኢትዮጵያን ለመግደል ያሴሩበት እና ልጆች በእናታቸው ላይ ቢላዋ የሳሉበት ዕለት በመሆኑ በሀዘንና በሱባኤ እንጂ በድግስና በጭፈራ የሚታሰብ ዕለት አይደለም። ሲነሳ ምንም ይሁን ምን ዛሬ በደረስንበት ሁኔታ ሲገመገም፣ ኢትዮጵያ በታሪኳ ውስጥ ህወሓትን የመሰለ መሠሪና አድርባይ ድርጅት ገጥሟት አያውቅም። እነሆ ዘንድሮም ይኸው አድርባይ ድርጅት የመሪዎቹን የሀብትና ዝና ረሀብ ለማስታገስ ሲል ያልነበረ ታሪክ እየፈጠረ በድግስ ስም ከድሀው ገንዘብ እየሰበሰበ ለሀብታም የህወሓት አባላትና ደጋፊዎች ያሸጋግራል። የድግሶቹ ሁሉ አዘጋጆች፣ እቃ አቅራቢዎችና ተጠቃሚዎች ራሳቸው የህወሓት መሪዎችና አሽቃባጮቻቸው ሲሆኑ ከፋዩ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። በህወሓት ድግስ የሚባክነው የሕዝብ ሀብት ስንት ሆስፒታል ይገነባ እንደነበር ስናስብ እና ይህ ሀብት በተገቢው ቦታ ውሎ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ስም ብቻ የያዙ ዩንቨርስቲዎቻችንን ትምህርት መቅሰሚያ ማድረግ እንችል እንደነበር ስናሰላ ሀዘናችን ጥልቅ ነው። ህወሓት ለልጅ ልጆቻችን የሚተርፍ ዕዳ እየቆለለ ዳንኪራ ሲረግጥና ሲያስረግጥ ማየትና መስማት ህሊና ሊሸከመው ከሚችል በላይ ነው።

አርበኞች ግንቦት 7፡ የአንድነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በህወሓት ወታደራዊ ሰልፍ እና የመሣሪያዎች ትዕይንት የሚረበሽ ድርጅት አይደለም። ይልቁንም በሰልፉ ጩኸት የታፈነው የኢትዮጵያዊ ወታደር ጩኸት ይሰማዋል። ኢትዮጵያዊ ወታደር በአዛዦቹ ላይ ጥርሱን ነክሶ፣ ቂም አርግዞ ሰልፉቸውን እንደሚሰለፍ አርበኞች ግንቦት 7 ያውቃል። አርበኞች ግንቦት 7፣ የሠራዊቱ አባላት ውስጥ ውስጡን እየተሰቃዩ የታዘዙትን መፈፀማቸው መብቃት አለበት ይላል፤ ወይ ተቀላቀሉን፣ አሊያም እውስጡ ሆናችሁ ሥርዓቱን የማዳከም ሥራዎችን ሥሩ። በእናንተ ውርደት የዘራፊዎች፣ ሙሰኖች፣ ጎጠኞችና ዘረኞች ደረት አብጦ መታየት የለበትም።

አርበኞች ግንቦት 7፣ የዘንድሮው የህወሓት 40ኛ ዓመት በዓል የጨረሻው በዓል እንዲሆን፤ ከርሞም ተመሳሳይ አዋራጅ በዓል እንዳናከብር፤ ሠራዊቱ በዘራፊዎች ታዞ የሚሰለፍበት ውርደት እንዲያበቃ ተባብረን ህወሓትን እንቅበር ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## ፕሬዜዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ወያኔ ሲሰነዘርባቸው

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

የህዋሃት መሪዎች ሲፈጠሩ በኢትዮጵያ አጀንዳ እንዳልነበር መለስ ብለው ታሪክን እያነሱ የህወሃትን ማኒፌስቶ እያጣቀሱ የተናገሩት ፕሬዜዳንት ኢሳያስ በዚያን ወቅት የነበረው የወያኔ ፍልስፍና የትግራይ ህዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት አለው የሚል እንደነበር አጋልጠዋል። አያይዘውም ዘረኛው የህወሃት የኢትዮጵያ ህዝብን በማወናበድ የአገዛዝ እድሜውን ለማርዘም ይረዳው ዘንድ ኢሃዴግ የሚል ጭንብል ያጠለቀበት መንገድ ተገቢ እንዳልነበረ በወቅቱ መናገራቸውን አስታውሰዋል። የኢትዮጵያን ህዝብ አፋጥጨና ከፋፍየ የፌደራላዊ ስርአት ካባ አስለብሸ አስተዳድረዋለሁ የሚለው አስተሳሰብ ሊሰራ እንደማይችል ገና ከመነሻው መቃወማቸውን ተናግረዋል።

የፋሽስቱ ወያኔ ህገ መንግስትን በተመለከተ ህገ መንግስቱ የሻቢያ በተለይም የርሰዎ የአእምሮ ውጤት እንደሆነ ይወራል የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ ኢሳያስ ህገ መንግስት የጠባቦቹ የህወሃት ጭፍሮች የአእምሮ ውጤት መሆኑን አስረግጠው ተናግረዋ ል። ይልቁንስ እነሱ ናቸው የፃፉት፤ እነሱ ናቸው ያረቀቁት ወዘተ የሚለው ማስተባበያና ማደናገሪያ ህወሃቶች ህገ መንግስቱ ለአገርና ለህዝብ እንደማይበጅ እያወቁ የስልጣን ቆይታቸውን ለማርዘም እንዲረዳቸው በማሰብ ያረቀቁት ስለሆነ ህገ መንግስቱ ነገ ሊያስከትል የሚችለውን ከባድ አደጋ ስለሚያውቁ ራሳቸውን ከተጠያቂነት ለማዳን የፈጠሩትና የሰነዱት ታሪክ ስለሆነ የምንፀጸትበት ነገረ የለም ሲሉ አስረድተዋል።

## በኦሮሚያ ክልል ቱባ ሹማምንት መካከል የተፈጠረው

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዓለማየሁ አቶምሳ ከኦህዴድ ሹማምንት ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ተመርዞ መገደሉ ይታወሳል። በሌላ ዜና ከሰሞኑ የፋሽስቱ ወያኔ ቱባ ሹም የሆነው አባዱላ ገመዳ አሜሪካን አገር ከሚገኝ የትምህርት ተቋም እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ድረስ በገንዘብ መግዛቱ በማስረጃ የተጋለጠ ሲሆን ይህም ከሌላኛው የህወሃት ቱባ ሹም ከቆስጠንጥኒዎስ ቀጥሎ በሁለተኛነት የተጋለጠ ቅጥረኛ አድርጎታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ዙሪያ ሊያካሂድ የነበረውን የመሬት ዘረፋ ተከትሎ በክልሉ በተቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃውሞ ቁጥራቸው ከ 60 በላይ የሆኑ ንፁሃን ዜጎች በወያኔ አጋዚ ጦር በአደባባይ በጥይት ተደብድበው መገደላቸውና በህዝባዊ ተቃውሞው ምክንያት የመሬት ዘረፋው መስተጓጎሉ የሚታወስ ሲሆን ከሰሞኑ የእብሪተኛው ወያኔ ቱባ ሹም የሆነው አባይ ጻሃየ የክልሉን ህዝብ በሐይል በማፈን የመሬት ቅርምቱን ለማስጀመር መዘጋጀታቸውን ዛቻ በተቀላቀለበት ሁኔታ መናገሩ ኢትዮጵያውያንን ክፉኛ አስቆጥቷል። የእብሪተኛው ወያኔ ቱባ ሹም የሆነው አባይ ጻሃየ ለክልሉ ህዝብ እንዲሁም ለአንዳንድ የኦህዴድ ካድሬዎች ጭምር ያለውን ንቀት ጸያፍ ቃላትን በመጠቀም የገለጸ ሲሆን በመጨረሻም በተለይም የክልሉን ህዝብ "ልክ እናስገባቸዋለን" ሲል መዛቱ የሰሞኑ መነጋገሪያ ሆኖ መሰንበቱ ታውቋል።

# ድል የአላማ ጽናት እንጂ የመሳሪያ ጋጋታ ዉጤት አይደለም

ጣሊያን ዋና ከተማ ሮም ዉስጥ ዋና ከተማዋን ከተለያዩ የጣሊያን ከተሞችና ጣሊያንን ከፓሪስ፤ከሙኒክ፤ከጄኔቫና ከቪዬና ጋር የሚያገናዉና በአመት ከ 150 ሚሊዮን በላይ መንገደኞችን የሚያስተናግድ አንድ ትልቅ የባቡር መስመር አለ። ይህ የባቡር መስመር የሚጠራዉ ሮማ ተርሚኒ እየተባለ ሲሆን የባቡር መስመሩ አድራሻ ደግሞ የአምስት መቶዎቹ አደባባይ በመባል ይታወቃል። ወደዘህ ትልቅ ባቡር መስመር ሲገባ አንድ እጅግ በጣም ትልቅ ሀዉልት ወለል ብሎ ይታያል፤ ይህም ሀዉልት የአምስት መቶዎቹ አደባባይ ወይም ፒያዛ ዴ ቺንኮቼንቶ በመባል የታወቃል። የፒያሳ ዴ ቺንኮቼንቶ መታሰቢያ ሀዉልት የተሰራዉ ወራሪዉ የጣሊያን ጦር አገራችንን ለመወረር ሲመጣ ዶጋሌ ላይ በራስ አሉላ ጦር የተገደሉትን አምስት መቶ የጣሊያን ወታደሮች ለማስታወስ ነዉ። በ1877 ዓም ዘመናዊ መሳሪያ ታጥቆ ጦርና ጎራዴ በታጠቀዉ የራስ አሉላ ጦር ዉርደት የተከናነበዉ የጣሊያን ወራሪ ሠራዊት ብድሩን ለመመለስ በ1888 ዓ.ም ብዛት ያለዉ ካባድ መሳሪያ፤ መድፍና መትረየስ ታጥቆ አድዋ ድረስ ቢመጣም በዳግማዊ ሚኒሊክ የተመራዉ ጀግናዉ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደገና ዉርደት አከናንቦት በጥቁር ህዝብ ታሪክ ዉስጥ ትዝታዉ ምንግዜም የማይደበዝዝ ድል አስመዝግቧል። የኢትዮጵያ ሠራዊት ዶጋሌና አድዋ ላይ እስካፍንጫዉ የታጠቀዉን የጣሊያን ወራሪ ጦር ደጋግሞ ያሸነፈዉ በመሳሪያ በልጦ ወይም የተሻለ የዉትድርና ችሎታ ስለነበረዉ ሳይሆን ከወራሪዉ ጦር የበለጠ ቆራጥነትና የአለማ ጽናት ሰለነበረዉ ነዉ።

በሃያኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን የተደረጉ ሌሎች የነጻነት ትግሎችን ስንመለከት በወቅቱ የአየር ኃይል ያልነበራት ትንሿ አገር ቬትናም በባህር፤ በአየርና በየብስ ጦርነት የገጠማትን ትልቁን የአለማችን ሀይል አሜሪካንን አሸንፋ ነፃነቷን ያስከበረችዉ በመሳሪያ ጋጋታ ሳይሆን የዛፍ ላይ ቅጠልና የተቦጫጨቀ ጨርቅ በለበሱ ነገር ግን ከፍተኛ የአላማ ጽናት በነበራቸዉ ጀግኖች ልጆቿ አማካይነት ነዉ።

አለማችን ትልቅ የጦርነት አዉድማ ናት ቢባል አባባሉ እምብዛም ከእዉነት የራቀ አባባል አይደለም። በእርግጥም አለም የጦርነት መድረክ ናት። ወደድንም ጠላን ወይም ብናምንም ባናምንም ጦርነቶች ሁሉ የተካሄዱት የህዝብን ነፃነት በሚደፍሩ ኃይሎችና መብቴንና ነጻነቴን አትንኩ በሚሉ ኃይሎች መካከል ነዉ። የአለማችን ታሪክ ወለል አድርጎ እንደሚያሳየን ደግሞ ይዋል ይደር እንጂ ሁሉም ዘለቄታዊ ድሎች የተመዘገቡት የአላማ ጽናት ባላቸዉ መብቴንና ነጻነቴን አትንኩ በሚሉ ኃይሎች ነዉ እንጂ የመሳሪያ ጋጋታ በተሸከሙ ኃይሎች አይደለም። የመሳሪያ ጋጋታ የተሸከመና ብዛት ያለዉ ወታደር ያሰለፈ ነገር ግን ለምን እንደሚዋጋ የማያዉቅና የአላማ ጽናት የሌለዉ ሠራዊት ግዜያዊ የጦር የጦር ሜዳ ድል ለያገኝ ይችላል፤ ሆኖም ጦርነቱን አሸንፎና የህዝብን ነጻነት ቀምቶ መዝለቅ በፍጹም አይችልም።

የአለም ታሪክ በነጭ ወረቀት ላይ በጥቁር ቀለም ቁልጭ አድርጎ የጻፈዉ አንድ ግዙፍ ሀቅ ቢኖር እልፍ ታንክና እልፍ አዕላፋት መድፎች ቢታጠቁም አምባገነኖች ለግዜዉ እንደተቆጣ ነብር ያስፈራሉ እንጂ ህዝባዊ አለማና ጽናት ያለዉ ጦር ፊት ሲቆሙ ፀሐይ እንደገላመጠዉ በረዶ ሚሸሸዉ የሚጠፉ ደንባራ ፈረሶች ናቸዉ። ለዚህም ነዉ ህዝብ አምባገነኖችን የወረቀት ላይ ነብር እያለ የሚጠራቸዉ።

ዛሬ ዕድሜዉ 35 እና ከዚያም በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚኒልክን ቤ/መንግስት ተቆጣጥረዉ የረገጡትን፤ የገደሉትንና መብቱንና ነጻነቱን ገፍፈዉ ያዋረዱትን ሁለት የወረቀት ላይ ነብሮች ያስታዉሳል የሚል ሙሉ እምነት አለን። ደርግ በ1967 ዓም "ያለ ምንም ደም እንከኗ ይዉደም" እያለ ወደ ሥልጣን ሲመጣ በፊዉዳሉ ስርዐት ጀርባዉ የጎበጠዉን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ደስ አሽኝቶ ነበር። እየቆየ ሲሄድና የተደበቀ ትክክለኛ መልኩ አደባባይ ሲወጣ ግን ያንን "ያለ ምንም ደም" የሚለዉን መፈክሩን ረስቶ ኢትዮጵያን የደም ገንዳ ሲያደርጋት በኢትዮጵያ ህዝብ ተጠልቶ አይንህን ለአፈር ተባለ። በሩሲያ ሰራሽ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች አስካፍንጫዉ የታጠቀዉና በቁጥሩና በወታደራዊ ብቃቱ አፍሪካ ዉስጥ ትልቁን ሠራዊት የገነባዉ ደርግ "እንደ ዉኃ የሚያጥለቀልቅ ኃይል አለኝ" እያለ ቢፎክርም እሱ እራሱ ተጥለቅልቆና በያለበት ተሸንፎ አገራችን ኢትዮጵያን ለዘረኛ አምባገነኖች ያስረከበዉ ለእግሩ ጫማ ለወገቡ መታጠቂያ በሌለዉ የገበሬ ጦር ተሸንፎ ነዉ። ደርግ እንደታጠቀዉ መሳሪያ ብዛት፤ እንዳደራጀዉ ወታደራዊ ብቃትና እንደ ወታደራዊ መሪዎቹ ችሎታ ቢሆን ኖሮ ደርግን እንኳን ተዋግቶ ለማሸነፍ በዉግያ ለመግጠምም የሚያስብ ኃይል በፍጹም አይነሳም ነበር፤ ነገር ግን ድል ምን ግዜም ቢሆን የመሳሪያ ጋጋታ ዉጤት ሳይሆን የራዕይ ጥራትና የአላማ ጽናት ዉጤት በመሆኑ በወቅቱ ይህንን የተገነዘቡ ኃይሎች ህብረትና አገር ዉስጥ የተቀሰቀሰዉ ህዝባዊ ቁጣ አንድ ላይ ሆነዉ ደርግን ጠራርገዉ የታሪክ ቆሻሻ ዉስጥ ሊጨምሩት ችለዋል።

ዛሬ ደርግን አሸንፈዉ ደርግ የተቀመጠበት ወንበር ላይ የተቀመጡት ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የአገርን ኃብት ከመዝረፍ፤ የተቃወማቸዉን ከመግደልና የኢትዮጵያን አንድነት ከማፍረስ ዉጭ እንዴትና ለምን ደርግን የመሰለ ሠራዊት እንዳሸፉ የተገነዘቡ አይመስልም። ወያኔዎች ደርግ ከወደቀ ከ24 አመት በኋላ ዛሬም በየቀኑ ደርግን ቢኮንኑም ተቀምጠዉ አገር የሚገዙት ልበቢሱ ደርግ የተቀመጠበት ወንበር ላይ ነዉና የደርግ በሽታ ተጋብቶባቸዉ እነሱም እንደደርግ ልበቢሶች ሆነዋል።

ኢትዮጵያ በየዘመኑ እያደገና እየዘመነ የመጣ፤ ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የተዉጣጣና ሞያን፤ ችሎታንና ወታደራዊ ሳይንስን አዳብሎ የታጠቀ ዘመናዊ የአገር መከላከያ ተቋም የነበራት አገር ነበረች። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች አዲስ አበባን ሲቆጣጠሩ ይህንን ዘመናዊ የአገርና የወገን መመኪያ የሆነ ሠራዊት አፍርሰዉና በየበረሃዉ ለእናት አገሩ የተዋደቀዉን ሰራዊት ለማኝ አድርገዉት ነዉ እነሱ ወርቃማዉ ዘር ብለዉ በሚጠሩት ዘር የበላይነት ላይ የተመሰረተ የመከላከያ ተቋም የገነቡት። ወያኔ የገነባዉ የመከላከያ ተቋም ባለፉት ሃያ አራት አመታት ዉስጥ አዲስ አበባ፤ ኦጋዴን፤ ጋምቤላ፤ ደቡብ ኦሞና በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች የወሰዳቸዉን ፀረ ህዝብና ፀረ አገር እርምጃዎች ስንመለከት ተቋሙ እዉነትም ለአገር ጥበቃ ሳይሆን የወያኔን የበላይነት ለማረጋገጥ የተቋቋመ ኃይል መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይችላል።

ይህ ሙሉ በሙሉ በትግርኛ ተናጋሪዎች የሚታዘዘዉ መከላከያ ሠራዊት ጋምቤላና ኦሞ ሸለቆ ዉስጥ ገበሬዉ ከቀዬዉ ተፈናቅሎ መሬቱ ባዕዳን ሲቸበቸብ አፉን ዘግቶ እንዲመለከት አድርጓል። ይሄዉ ሠራዊት በ1997 ዓም በአግአዚ ነብሰ ገዳዮች እየተመራ የህዘብ ድምጽ ይከበር ያሉ ከ200 በላይ ሠላማዊ ዜጎችን በግፍ ጨፍጭፏል፤ ከዚህ በተጨማሪ የወያኔ መከላከያ ሠራዊት ኦጋዴንና ጋምቤላ ዉስጥ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽሟል አሁንም እየፈጸመ ነዉ። እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ትኩረት ሰጥቶ ሊመለከተዉ የሚገባዉ ነገር አለ፤ እሱም ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ልማታዊ ሠራዊት ብለዉ እያሞካሹና "የመከላከያ ኃይሎች ቀን" የሚል ስያሜ ሰጥተዉ በየአመቱ ማክበር የጀመሩት በዐል የሚያወድሰዉ ይህንኑ አንድነቱንና ነፃነቱን እጠብቃለሁ ብሎ ቃል ኪዳን የገባለትን ህዝብ ያለ ርህራሄ የሚጨፈጭፈዉን የወያኔ ሠራዊት ነዉ። በተለይ ወያኔ ባለፈዉ ሳምንት ባህር ዳር ዉስጥ ያለ የለሌ የመሳሪያ ጋጋታዉን አደባባይ አዉጥቶ ለህዝብ እያሳየ ባከበረዉ የመከላከያ ቀን በዐል ለህዝብ ማስተላለፍ የፈለገዉ መልዕክት ቢኖር "ይህንን እያያችሁ ከወያኔ ጋር በእሳት አትጫወቱ " የሚል የሞኝ መልዕክት ነዉ።

ይህ ባህር ዳር ላይ የተላለፈዉ መልዕክት ለማን እንደሆነና በተለይ ባህር ዳር የመልዕክቱ ማስተላለፊያ ቦታ ሆና የተመረጠችበት ምክንያት ለማንም ኢትዮጵያዊ ግልፅ ይመስለናል። የዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች መሰባሰቢያ የሆነዉ ህወሓት የተወለደዉም ሞቶ የሚቀበረዉም ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ መሆኑን እሱም ደጋፊዎቹም ካወቁ ቆይቷል። ዉቧና የጀግኖች መፍለቂያ የሆነችዉ ባህር ዳር ደግሞ ይህንን የወያኔን የቀብር ጉዞ ከጀመረች አመታት አስቆጥራለች። እንገዲህ ወያኔ በየቀኑ ከባድ መሳሪያና ስፍር ቁጥር የሌለዉ ወታደር ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የሚያጓጉዘዉ ከዚሁ ከማይቀርለት ዉድቀቱ የሚያድኑት እየመሰለዉ ነዉ። እዚህ ላይ አንድ ወያኔ በፍጹም ያልተረዳዉ ነገር ቢኖር ህወሓትን ከኢትዮጵያ ምድር ጠራርጎ የሚያጠፋዉና ግብዐተ መሬቱን የሚፈጽመዉ ይሄዉ ወያኔ በነጋ በጠባ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የሚያጓጉዘዉ ሠራዊት መሆኑን አለመረዳቱ ነዉ። የወያኔ አይን ያወጣ ዘረኝነት በከፍተኛ ደረጃ ከተንጸባረቀባቸዉና በየቀኑ በዘረኝነት እሳት ከሚለበለቡ የህብረተሰብ ክፍሎች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ የመከላከያ ሠራዊት ነዉ። ይህ ሰራዊት እንደ መሬት የሚረግጡትን የወያኔን አለቆቹን ትዕዛዝ ተቀብሎ ከታሰረበት የዘረኝነት እስር ቤት ነፃ ሊያወጡት በሚታገሉ የኢትዮጵያ ህዝብ የነጻነት ኃይሎች ላይ መሳሪያዉን ያዞራል ብሎ የሚያምን ኢትዮጵያዊ ያለ አይስለንም፤ በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔን የመሳሪያ ጋጋታ አይቶ ለእናት አገሩ አንድነትና ለኢትዮጵያዉያን ወገኖቹ ነጻነት ህይወቱን ከመስጠት ወደ ኋላ የሚል ኢትዮጵያዊ ቢኖር እሱ ከወያኔ ጋር በጥቅም የተጋባ ከሃዲ መሆን አለበት። የኢትዮጵያ ህዝብ ምንግዜም ቢሆን በወሬ ቱማታና በመሳሪያ ጋጋታ ትጥቁን ፈትቶ አያዉቅም። በ1930ዎቹ ፋሺስት ጣሊያኖችንና በ1970ዎቹ ወታደራዊዉን ደርግ ተዋግቶ ያሸነፈዉ እነዚህ ኃይሎች የታጠቁትን መሳሪያ እየቀማ በተዋጋቸዉ ነጻነት የጠማዉ ኃይል ነዉ። የዛሬዎቹ የወያኔ ፋሺስቶች እጣም ጣሊያንና ደርግ ከገጠማቸዉ ሽንፈት የተለየ አይሆንም።

የአገራቸዉን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከጠላት ለመከላከል የመከላከያ ሠራዊትን የተቀላቀሉ የኢትዮጵያ ልጆች "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" የሚለዉን የአባቶቻቸዉ ምሳሌያዊ አባባል ምንነት በሚገባ የሚረዱ ይመስለናል። ስለሆነም ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በዘር ለይቶ እየረገጣቸዉ፤ እያዋረዳቸዉና ከሰዉ በታች አድርጎ እየተመለከታቸዉ ይህንን ቅጥ ያጣ በደል ለማረሳሳት የመከላከያ ቀን እያለ በሚያከብረዉን የይስሙላ በዐል እንድም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባል ሊታለል አይገባም። ከአግአዚ ነብሰ ገዳዮች ዉጭ ያለዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት እንደማንኛዉም የወያኔ እስረኛ እንደሆነ የህብረተሰብ ክፍል ነፃ መዉጣት የሚገባዉ ክፍል ነዉ። ይህ የህዝብ ወገን የሆነዉ የመከላከያ ሠራዊት ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

# አባይ ወልዱና ሳሞራ የኑስ የህወሃት ክንፍ እንዲፈጠር አሲራቸኋል በሚል ተገመገሙ

በቤተመንግስት ትንሹ አዳራሽ ውስጥ የወያኔ .ኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣናትን መገምገም የጀመረዉ ጉባኤ የትግራይ ክልል ፕሬዚዳንት አባይ ወልዱ የህወሃት ክንፍ እንዲፈጠር ከመከላከያ ኢታማጆር ሹም ከሳሞራ የኑስ ጋር አስራቸኋል የሚል ጠንከር ያለ ሂስ እንደቀረበባቸዉ ግምገማዉን በቅርብ የቃኙት የግንቦት ሰባት ምንጮች ገለጹ። አባይ ወልዱ የቀረበበትን ሂስ በደፈናው ተቀብያለሁ፣ አርማለሁ በማለት መመለሱን ተያይዞ ደረሰን ሰነድ ያስረዳል። አባይ ግለሂሱን እንዲያወርድ ሲጠየቅ የስራ ሰአት የማክበርና ከአሉባልታ ወሬ ጋር በተያያዘ ችግር እንዳለበት የተናገረዉ አባይ ወልዱ በ1 ለ5 አደረጃጃት እንደማይሳተፍም ተናግሯል። አብረዉት ግምገማ የተቀመጡት በየስራ ባልደረቦቹ በበኩላቸው " አስተያየት የመቀበል ችግር አለብህ፣ በረባ ባልረባው ከስራ ገበታህ ትቀራለህ፣ ችግሮችን በውይይት የመፍታት እጥረት አለብህ፣ የሰራሃውን ስራ በጊዜ የማምጣት ችግር አለብህ፣ ህጎችን የማክበር ችግር ይታይብሃል" በማለት ገምግመዋቸዋል። አቶ አባይ በአጠቃላይ ግምገማየ " ቢ" ውጤት ማግኘታቸውም በሰነዱ ተመልክቷል።

ግምገማው የተካሄደው እንደተለመደው ባለስልጧናቱ በየተራ አስቀድመው ችግራቸውን እንዲናገሩ በማድረግና የራሱን ችግር በተናገረው አመራር ላይ ሌሎቹ ያላቸውን ተጨማሪ ትችት እንዲያቀርቡ በማድረግ ነው። በአቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ መሪነት በተካሄደው በዚህ ግምገማ ከ አዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ የተገመገሙት አፈ-ጉባኤ አባዱላ ገመዳ፣"የሀሰት የስራ አፈጻጽመ ታቀርቢያለሽ" የተባሉት የሴቶችና የወጣቶች ሚኒስትር ዘነቡ ታደሰ፣"ሳሞራን ትፈራዋለህ"ተብለው የተገመገሙት የመከላከያ ሚኒስትሩ ሲራጅ ፈርጌሳ፣"ኮምፒዩተርና ሞባይል ላይ ጥብቅ ትላለህ" የተባሉት አቶ ሬድዋን ሁሴን፣"ከባልደረቦችሽ ጋር ትጋጫለሽ"የተባሉት ወይዘሮ አስቴር ማሞ፣ የማንበብ ችግር አለብኝ ያለዉ ዶክተር ካሲ አሊላ"ፈሪ ነህ" የተባለ ሲሆን፣ "ከደባል ሱስ የጸዳህ አይደለህም"የተባሉት የገንዘብ ሚኒስትሩ ሶፊያን አህመድ እና ሌሎች በርካታ ባለስልጣናት " ሲ" አግኝተዋል።

የጠ/ሚኒስትሩ የጸጥታ አማካሪ የሆነዉ የቀድሞው የትግራይ ክልል ፕ/ት ጸጋየ በርሄ ደግሞ " የማሳቀድ ፣ በንባብ ራስን የማብቃትና በጥራት የማሰራት እጥረት አለብኝ" በማለት ግለ-ሂሱን ያወረደ ወይም ራሱን የገመገመ ሲሆን፣ ጓደኞቹ ደግሞ " ሞጋች የሆኑ ነገሮችን ያለመንካት ችግር አለብህ፣ አስተባብሮ የመስራት እጥረት አለብህ፣ ሌሎችን አሳቅዶ የመስራት እጥረት አለብህ፣ ሰአት አታከብርም፣ ውሳኔ የመስጠት ችግር አለብህ፣ የክትትልና ቁጥጥር እጥረት ይታይብሃል" በሚል ሂስ ሰጥተዉበታል። ጸጋየ በርሄ ለቀረበበትን አስተያየት ተቀብየዋለሁ ያለ ሲሆን በአጠቃላይ ግምገማዉ "ቢ" ተሰጥቶታል። ዶ/ር ካሱ ኢላላ በበኩሉ የማንበብ እጥረት አለብኝ በማለት ራሱን የገመገሙ ሲሆን፣ ሎሎች ባልደረቦቻቸው ደግሞ " የስልክ አጠቃቀም ችግር አለብህ፣ ወሬ የመስማት፣ የማኩረፍ ችግር አለብህ፣ የቢሮ ስነምግባር አለማክበር ይታይብሃል፣ ፈሪ ነህ፣ ግንባር ቀደም አይደለህም፣ ሰርቶ የማሰራት እና የመምራት ችግር አለብህ፣ ለተተኪዎች አይንህ ደስተኛ አይደለም" በሚል ተገምግመዋል። ዶ/ር ካሱ ኢላላ ሂሱን መቀበሉን የገለጸ ሲሆን በአጠቃላይ ግምገማዉ "ሲ" ውጤት ተሰጥጥቶታል። አቶ አርከበ እቁባይ ደግሞ በቁጭትና በእልህ የመስራት እጥረት አለብኝ፣ ስራን አድምቶ የመስራት እጥረት አለብኝ፣ ሰአት ማክበር፣ በቡድን መስራት ላይ ውስንነቶች አሉብኝ በማለት ራሱን የገመገሙ ሲሆን፣ ሌሎች ጓደኞቻቸው ደግሞ ስራን የማዘግየት ችግር አለብህ፣ ከስራ ባልደረቦች ጋር ተግባብቶ የመስራት ችግር አለበት፣ ነገሮችን አግዝፎ የማየት፣ ቂመኛነት አለበት፣ ለችግሮች መፍትሄ የመሻት እጥረት አለብህ፣ ግጭትን ያለማርገብ ችግር አለብህ" በሚል ተገምግሟል።

የመከላከያ ሚኒስትሩ ሲራጅ ፈርጌሳ አቅዶ የመስራት ክፍተት አለብኝ፣ ራስን በማያቋርጥ የንባብ ባህል የማብቃት እጥረት አለብኝ በማለት ራሳቸውን የገመገሙ ሲሆን፣ ባልደረቦቻቸው ደግሞ " በንባብ ራስን የማብቃት ችግር አለብህ፣ አሳምኖ የማሰራት እጥረት አለብህ፣ ለሌሎች ሀሳብ የመስጠት ቁጥብነት አለብህ፣ ያለህን እውቀት ለሌሎች የማጋራት እጥረት አለብህ፣ ሳሞራን ትፈራዋለህ፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤትህ ያለው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ደካማ ነው" በሚል ተተችተዋል። አቶ ሲራጅ መከላከያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ደካማ መሆኑን ፣ ችግሩ በመስሪያ ቤቱ ብቻ ሳይሆን በጦሩም እንደሚታይ ገልጸው፣ አደረጃጀት ለመፍጠር ቢሞክሩም የሚተባበራቸው አመራር ማጣታቸውን፣ ከሳሞራ ጀምሮ ሃይለማርያምም እንደሚያውቅ" ተናግረው፣ ሌሎች የተነሱት ሃሳቦች ገንቢ ናቸው፣ ተቀብያቸዋለሁ ብለዋል። የኦሮምያ ም/ል ፕ/ት የሆኑት ወ/ሮ አስቴር ማሞ በበኩላቸው "የስራ ሰአት እሸራርፋለሁ፣ ስሜታዊነት አለብኝ፣ በአንድ ለአምስት ላይ ክፍተት አለብኝ" በማለት ራሳቸውን የገመገሙ ሲሆን፣ ሌሎች የምክር ቤት አባላት ደግሞ " ተግባብቶ የመስራት እጥረት አለብሽ፣ ከስራ ማርፈድ፣ መቅረት አለብሽ፣ የቢሮ ሰአት አታከብሪም፣ ትሸራርፊያለሽ፣ ከባልደረቦችሽ ጋር ትጋጫለሽ፣ በቢሮው ውስጥ ሶስት የአካባቢሽን ልጆች አዲስ አበባ በአጠቃላይ ዘጠኝ የሚደርሱ በሚኒስትር ቢሮዎች በሹመት እንዲመጡ አድርገሻል " የሚል አስተያየት ሰጥተዋል። ወ/ሮ አስቴር ሰዎቹ የመጡት በእርሳቸው ትእዛዝ መሆኑን፣ ነገር ግን ሰዎቹ ከአቅም በታች ናቸው ማለት እንደማይቻልና፣ ሁላችንም በተመሳሳይ መንገድ በችሎታቸው ያመጣናቸው አሉ ሲሉ ተከላክለዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ ሶፍያን አህመድ ደግሞ ስራን በፍጥነት የመፈጸም እጥረት አለብኝ ብለው ራሳቸውን ሲገመግሙ፣ ሌሎች ባልደረቦቻቸው ደግሞ "ከደባል ሱስ የጸዳህ ብትሆን፣ ስራ ያዘገያል፣ ስራን ለነገ ባትል፣ ራስህን ከሌሎች ማራቅህ ብተተው" በሚል ገምግመዋቸዋል። የሴቶችና የወጣቶች ሚኒስትር ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ በበኩላቸው የስራ ሰአት መሸራረፍ አለብኝ፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የታቀደውን ያህል አልሰራሁም በሚል ስለድክመታቸው ሲናገሩ፣ ሌሎች የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው " ለኢህአዴግ ተልእኮ አስፈላጊ ነገሮችን ጠይቆ ማሟላት ላይ እጥረት አለብሽ፣ ይሉንታ ያጠቃሻል፣ ሴቶች ተሳትፎ ስራው ላይ እንዲሻሻል የጎላ ድርሻ አልተወጣሽም ፣ ክፍት ሚኒስቴር ነው ማለት ይቻላል፣ የሃሰት አፈጻጸም እና ሪፖርት ታቀርቢያለሽ" በሚል ገምግመዋታል። ወ/ሮ ዘነቡ "የተሰጠኝ አስተያየት ገምቢ ነው ወደ ፊት አየዋለሁ፣ ሂሱን ወስጀዋለሁ" ብለዋል። ሽፈራው ሽጉጤ ደግሞ "የስራ ሰአት አለማክበር ብቻ ሳይሆን ትቀራለህ፣ ስብሰባ ላይ አትገኝም፣ አማራን ባስወጣህበት የደቡብ ክልል መስተዳደር ጊዜህ ለክልሉ ነዋሪዎች ነፍጠኛ ከኛ ይወገዳል ብለህ ተናግረሃል" በሚል ከብአዴን ተወላጆች አስተያየት ቢሰጥም፣ አቶ ሽፈራው " ከጠ/ሚኒስትሩ የተሰጠኝን ተልእኮ ነው በአግባቡ የተወጣሁት፣ ሌላ አልጨመርኩም አላስወጣሁም" ብለው መልሰዋል። የአማራ ክልል ም/ል ፕሬዚዳንት እና የብአዴን ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ አለምነው መኮንን "የመለስን ቦታ የመተካት ህልም አለህ፣ የስልጣን ጥመኝነት አለብህ፣ የድርጅቱን ህልውና አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ ተንቀሳቅሰሃል፣ ከመለስ ውጭ ሌላው የሞተ ነው ብለህ ተናግረሃል፣ ሆን ብለህ ለኢሳት መረጃ እንዲደርስ ታደርጋለህ፣ የብሄሮችን እኩልነት አትቀበልም፣ የስልጣን ሰንሰለት በጎጠኝነት መስርተሃል፣ አጉል ጀብደኝነት አለብህ" ተብለው ሲገመገሙ፣ እርሳቸው ግን ከተሰጠኝ ተልእኮ ውጭ አልተንቀሳቀስኩም፣ ነገሩን አጣመው የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ በማለት በብሄር እኩልነት አታምንም በተባሉት ላይ ከረር ያለ መልስ ሰጥተዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም ደግሞ "በእቅድ ላይ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ላይ ስኬታማ አይደለሁም፣ የስራ ሰአት አከባበር ችግር አለብኝ" ብለው ራሳቸውን የገመገሙ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ " ስራን የማዘግየት ችግር አለበት፣ በማህበራዊ ሚዲያ የግለሰቦችን ታሪክ ለራሱ ገጽታ ግንባታ አውላል፣ ለአብነትም ከአረብ አገራት የተመለሱ ሰዎችን፣ ከተሰጠው ተልእኮ ውጭ ይንቀሳቀሳል" ብለዋቸዋል። ዶ/ር ቴዎድሮስ ሂሱን እንደማይቀበሉት የቃለ ጉባኤ ሰነዱ ያሳያል።

የአፋር ክልል ፕሬዚዳንት እስማኤል አሊ ሴሮ " የንባብ ባህል እጥረት አለብኝ" ብለው ራሳቸውን ሲሄሱ፣ ሌሎች ደግሞ አርፍዶ የመግባት፣ ፈጥኖ የመውጣት ነገር ይታይበታል፣ እቅድ እና ቅድመ ዝግጅት ላይ እጥረት አለበት፣ ሰአት አለማክበር ይታይበታል" ብለዋቸዋል።

የፌደራል ሚኒስትሩ ዶ/ር ሽፈራው ተክለማርያም በበኩላቸው "ጥራት ያለው ስራ እሰራለሁ ብየ አላስብም፣ የንባብ ባህል ላይ ችግር አለብኝ፣ ሰአት እሸራርፋለሁ" ብለው ስለራሳቸው ድክመት ከተናገሩ በሁዋላ፣ ሌሎች ደግሞ " ስራ ሲታዘዝ እገሌ ሳይሰራ የማለት ባህሪ አለው ቢያስተካክል፣" ብለው ሲገመግሙዋቸው ዶ/ር ሽፈራው አልቀበለውም ብለዋል። ጉዳዩ እንደገና ይታይ የሚል ከቤቱ አስተያየት በመቅረቡ "ሌሎች እንደገና " የባህሪ ቁጡነት ይታይብሃል፣ አንድ ለአምስት አዘውትረህ አትሳተፍም፣ ይሉንታ አለብህ፣ አሁንም በከፍተኛ ደረጃ ያለውን አክራሪነት መቆጣጠር አልቻልክም" የሚል ሂስ አቅርበዋል። ዶ/ር ሽፈራው "ማህበረ ቅዱሳንን መንካት መሞት መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን፣ ከሱ ውጭ ያለውን ግን እየሰራሁ ነው።" ብለው መልስ ሰጥተዋል። አንዳንድ ሂሶችን መቀበላቸውን ተናግራል። ሩድዋን ሁሴን በኮሚኒኬሽን ስራ ተቃዋሚዎች እንዲበልጡን አስደርግሃል የሚሉና ሌሎች በርካታ ትችቶች ሲቀርቡባቸው፣ አባ ዱላ ገመዳ ደግሞ ከስራቸው እና በኦሮምያ ከሚታየው ችግር ጋር ተያይዞ ትችት ቀርቦባቸዋል።

**የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## በሙስሊሞች ላይ በከፍተኛ የደህንነት ሃይሎች የሚመራ የእስር ዘመቻ መከፈቱ ተነገረ

ፍትሕ ራዲዮ እንደዘገበው፤ በአዲስ አበባ ብቻ ከ800 - 1000 የሚደርሱ ሰዎችን ለማሰር ታቅዷል።

የሙስሊሙን ማህበረሰብ አካላት  በምክንያት ለማሰር በከፍተኛ የኢትዮጲያ መንግስት የደህንነት ሃይሎች የሚመራ ዘመቻ  መከፈቱን ፍትህ ራዲዩ ዘግቧል። ራዲዮው ምንጮቹን በመጥቀስ እንደዘገበው፤ ዘመቻው ያነጣጠረው፤ ከመጪው  ሃገራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ በህዝበ-ሙስሊሙ መካከል ትልቅ ንቅናቄ ይፈጥሩ ይሆናል የሚል ስጋት ባሳደሩ ሙስሊሞች ላይ ነው። መንግስት ምርጫው ከመድረሱ አስቀድሞ በሃገሪቱ እየተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በተለያዩ ምክንያቶች ሲያዳክምና ሲያግድ ከመቆየቱም በላይ የግል ፕሬስ ጋዜጠኞችን ለእስርና ለስደት መዳረጉ ይታወቃል።

በአሁኑ ወቅት ሳይታገዱ  የቀሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች ለኢህአዴግ ስጋት ሊሆኑ የሚችሉት በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ብቻ መንጠላጠል ከቻሉ ነው የሚል ግምገማ የወሰደው ኢህአዴግ፤ በዚህም መሰረት በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ የመጨረሻ የማዳከም ዘመቻ መከፈት አለበት የሚል ድምዳሜ ላይ  መድረሱ ተመልክቷል። በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎች የአሰሳ እና ስምሪት ተግባር እየተካሄደ ሲሆን፤በተለይ በአዲስ አበባና በጅማ በርካታ ሙስሊሞችን በጅምላ  የማሰሩ ዘመቻ ተጀምሯል። እንደ ምንጮቹ መረጃ፤ በከፍተኛ የደህንነት ሀይሎች በሚመራው በዚህ ዘመቻ፤ ሃገር አቀፍ ምርጫው ከመካሄዱ በፊት  በአዲስ አበባ ብቻ ቁጥራቸው ከ 800 እስከ 1000 የሚደርሱ  ሰዎችን ለማሰር እቅድ ተይዟል።

በዛሬው ዕለትም የራዲዩ ቢላል ጋዜጠኛ የነበረው ካሊድ መሐመድን ጨምሮ ቁጥራቸው እስካሁን በውል ያልታወቀ በርካታ ሙስሊሞች ከያሉበት በደህንነት ሃይሎች እየታፈኑ ወደ እስር ቤት እየተወሰዱ መሆናቸው ተመልክቷል። ሙስሊሞቹ በተያዙበት አካባቢዎች በወደሚገኙ የፖሊሰ ጣብያዎች እየታጎሩ ሲሆን፤ የመኖሪያ ቤታቸውም በፖሊሶች እና በደህንነቶች እየተፈተሸ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። ቤታቸው የሚገኙ የተለያዩ ላፕቶፕ እና የግል ንብረቶቻቸውም “ለምርመራ ያስፈልጋሉ” እየተባሉ በደህንነቶች  መወሰዳቸው ታውቋል።

## በህወሃት ውስጥ ፖለቲካዊ ጠባብነትና ትምክህት መኖሩን አቶ ስብሃት ተናገሩ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሰኘዉን የመናገርና እንዳሰኘዉ ሀሳቡን የመግለጽ ብቸኛ ነጻነት ያለዉ ስብሃት ነጋ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሐት) ውስጥ ፖለቲካዊ ጠባብነትና ትምክህት የሚያራምዱ ወገኖች መኖራቸውንና ሕገመንግስቱም በተሟላ ሁኔታ እየተተገበረ አለመሆኑን ተናገረ።  ስብሃት ነጋ የካቲት 9 እና 10/2007 ዓ.ም ከወጣው አዲስዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረገዉ ቃለምልልስ በህወሃት ውስጥ ፖለቲካዊ ጠባብነትና ትምክህት መኖሩን አምኗል። «ፖለቲካዊ ጠባብነትና ትምክህት በመንደራችን አለ። ቢሮክራሲው የጸዳ አይደለም። እንግዲህ ፓርቲውን የሚመራው መንግስት ነው። ተወዳዳሪና ቀና የሆነ ቢሮክራሲ ገና አልተገነባም። ከላይ እስከታች ሕገመንግስቱ በትክክል እየተተገበረ ነው ወይ የሚለው ጎዶሎ አለበት» ብለዋል። «የትግራይ ሕዝብ ጥያቄዎች ተመልሰዋል ወይ» በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ የሰጡት አቶ ስብሃት የመልካም አስተዳደር ችግር መኖሩን አረጋግጠው ችግሩን የምንፈታው ሕዝቡን ይዘን ነው ብለዋል። አይይዘውም «በአስተማማኙ ጎዳና እየተደረገ ያለው ሩጫ ዘገምተኛና እንከን ያለበት ነው። እንከን ስል ቢሮክራሲው የተሳለጠ ባለመሆኑና የቀናነት ጉድለት ስላለ ሕዝቡ በሚገባ ደረጃ እየተጠቀመ አይደለም። የተዛባ አመለካከትና የተንዛዛ አሠራር ይስተዋላል። ይህ ክፍተት መቀረፍ አለበት። ህወሃት/ኢህአዴግ ስህተቱን ይፋ የሚያደርግና የሚያርም ድርጅት ነው። ስለዚህ ከሕዝቡ ጋር በመተባበር ችግሮቹ ይፈታሉ የሚል እምነት አለኝ” ሲሉ ተናግረዋል። በ1993 ዓ.ም በልዩነት ህወሓትን ጥለው የወጡ የድርጅቱ ነባር ታጋዮች ጉዳይንም በተመለከተ ሚቹ የቀድሞ ጠ/ሚኒስትር አቶ መለስን በመደገፍና የእነስዬ አብርሃን ቡድንን በመንቀፍ  በሰጡት አስተያየት መነሻቸው የኤርትራ ጉዳይ ይሁን እንጂ ዋና ዓላማቸው የሥልጣን ጥማት ነው ብለዋል። «የሥልጣን ጥማቱ ታምቆ የቆየ ነው። ሻዕቢያ ኢትዮጵያን የመውረሩን ጉዳይ ያለመከታተላችን የሁላችንም ድክመት ነው። ቀደም ብለን ማወቅ ነበረብን የሚል እምነት አለኝ። ችግሩን ሰላማዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት የዲፕሎማሲ ጥረት ማድረግ ያስፈልግ ነበር። ለሰላም አሟጠን ዕድል እንስጥ፣ ዕድሉ ካላዋጣን መዋጋት ማን ይከለክለናል የሚሉ የአመራር አባላት ነበሩ። እኛ ከኢሳያስ ተሸለን መገኘት አለብን፤  የእኛ ሰዎች ግን እንደ ኢሳያስ ሆኑ። ነፋስ በኤርትራ መጣ ከተባለ እንዋጋ ነው የሚሉት። ከወላጆቻቸው በምንም አይለዩም። ስንወረር ዝም ብላችሁ አያችሁ የሚለውን እንደምክንያት ወስደው ቡድን ፈጠሩ»ብለዋል።

ተወልደ የህወሃት ምክትል ሊቀመንበር እያለ፣ ስዬም የመከላከያ ሚኒስትር እያለ ኤርትራ ነጻነትዋን ስታገኝ የአሰብ ወደብ ጉዳይ አብሮ ያለቀለት ነበር ያሉት አቶ ስብሃት፣ አሁን የአሰብ ጉዳይ እንደልዩነት የሚነሳው ሰበብ እንጂ ጉዳዩ ወንበር ፍለጋ ነው ሲሉ የእነስዬን ቡድን በሥልጣን ጥመኝነት ፈርጀዋል። ጡረተኛው አቶ ስብሃት በአሁኑ ወቅት እምብዛም እንቅስቃሴ የሌለውና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር የሚገኘው የሠላምና የልማት ዓለም አቀፍ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ናቸው። ይህ ስብሃት ነጋ ከሰሞኑ የሰጠዉ አስተያየት ምንም አዲስ ነገር አንደለሌለበትና እንዳዉም ስብሃት ነጋ እራሱ በዘረኝነት በተለያ በአማራዉ ህዝብ ጥላቻ ላይ ተንተርስሶ የዛሬ አርባ አመት የፈጠረዉን ድርጅት ዛሬ ጠባብነት ይታይበታል ማለቱ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ስብሃት ነጋ እራሱ የለየለት ጠባብ ሰዉ መሆኑን ብቻ ነዉ።

የእኛ፣ የአገራችንና ዜጓቿ ቀጣይ ዕጣ ፈንታ በሁለት አማራጮች ላይ የተንጠለጠለ ነው የሚለው ትብብሩ  አንድም ያለውን አምባገነናዊ ሥርዓት ተቀብለን፣የአገራችን ሉዓላዊነት በጥያቄ ውስጥ ባለበት፣ የጭቆና ቀንበር ተሸክመን በከፋ ውርደት ሥር ሰጥ- ለጥ ብሎ መገዛት፤ አሊያም– አምባገነንነትና ጭቆናን ‹‹በቃ›› በማለት በሕዝባዊ የተቀናጀ ሰላማዊ ትግል ለአገራችን ሉዓላዊነትና የዜግነት ክብራችንን ለማስመለስ በህገ መንግስታዊ መብታችን ተጠቅመን  ትግላችንን እስከማይቀረው ለውጥ/ ድል ደጃፍ ድረስ በቆራጥነት መቀጠል፣ ናቸው ብሎአል። ሁሉን አቀፍ የነጻነትና ክብርን የማስመለስ ሰላማዊ ትግል ለ9ኙ ፓርቲዎች ብቸኛ አማራጭ መሆኑንም ጠቅሰዋል። ፓርቲዎቹ በመጨረሻም በሚደረገው አገራዊ፣ ሰላማዊና ሕዝባዊ ትግል በማይቀረው የሥርዓት ለውጥ ለሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር በአንድነትና በቆራጥነት ህዝቡ እንዲነሳና በየካቲት 22 የተቃውሞ ሰልፍ ላይ እንዲገኝ በመግለጫቸው ጥሪ አቅርበዋል።

## ድል የአላማ ጽናት እንጂ የመሳሪያ ጋጋታ ዉጤት አይደለም

... ( ከገጽ 3 የዞረ )

እራሱን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቹንና እህቶቹን ጭምር ከወያኔ ዘረኝነት ነጻ ሚያወጣት አለበት። እስከቅርብ ግዜ ድረስ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት ብዙም አማራጭ ስላልነበራቸዉ አንገታቸዉን ደፍተዉ የጠላታቸዉን የወያኔን ትዕዛዝ እየተቀበሉ ሲፈጽሙ ቆይተዋል፤ አሁን ግን አንገታቸዉን ቀና አድርገዉ የወያኔን አንገት የሚያሰደፉበት አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። ዛሬ ለእናት አገራቸዉ ነጻነት በህይወታቸዉ ቆርጠዉ ብረት ያነሱ የነጻነት አርበኞች የመከላከያ ሠራዊት የወያኔ አለቆቹን ትዕዛዝ ላለመቀበልም ሆነ ወይም የታጠቀዉን መሳሪያ ወደ ጠላቱ ወደ ወያኔ ማዞር የሚችልበትን አመቺ ሁኔታ ፈጥረዉለታል።

ዉድ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት ሆይ ጨለማዉ ሊጠራ ሲል ይበልጥ ይጨልማልና ወያኔ ወደ ሰሜናዊዉ የአገራችን ክፍል የሚያጓጉዘዉ የመሳሪያ ጋጋታና የሠራዊት ብዛት በፍጹም ልትደናገጥ አይገባም። ወያኔን ካንተ በላይ በቅርብ የሚያዉቀዉ የለም፤ የወያኔ ኃይለኝነትና ትልቅ መስሎ መታየት አንተ በዉስጡ ስላለህበት ብቻ ነዉ። ስለዚህ ይህንን ፀረ ኢትዮጵያ ኃይል ለቅቀህ በያለህበት ላንተ፤ ለወገኖችህና ለእናት አገርህ ነፃነት መከበር ከቆረጡ ወገኖችህ ጋር በፍጥነት ተቀላቀል። ይህንን ማድረግ የማትችለዉ ደግሞ ወያኔ ከገዛ ወገኖችህ ጋር እንድትዋጋ ትዕዛዝ ሲሰጥህ የታጠከዉን መሳሪያ ወደ ወገኖችህ ሳይሆን ወደ ራሱ ወደ ወያኔ አዙር። ወያኔ ለትንሽ ግዜ የማይበገር መስሎ ሊታይ ይችል ይሆናል የማይቀረዉ የዘለቄታ ድል ግን ምን ግዜም የህዝብ ነዉ፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ደግሞ ትናንት አንደነበረ ሁሉ ዛሬም የኢትዮጵያ ህዝብ አለኝታ ነዉ።

**ድል የህዝብ ነዉ!**